

**eppf**

**Rahel Mamo**

https://www.facebook.com/profile.php?id=100016959071559

**Abiy and his ambivalent peace with Eritrea: Eritrean Role in Destabilizing Ethiopia**. 02 August 2019.17

በሀራችን ኢትዮጵያ ጠሚ አብይ ወደስልጣን ከመጣ ወዲህም ተጠናክሮ የቀጠለው እርስበርስ ግጭትና የስልጣን ሽኩቻ ብሎም ይህ እያስከተለው ያለው ቀውስ፣ አለመረጋጋት፣ መፈናቀል፣ ረሃብ፣ ህመም፣ የዜጎች ሞትና ስደት ሁሉ አቀጣጣይ የሆነው የኤርትራው መሪ EPLF እንደሆነ ለመገንዘብ አዳጋች አደለም።

ከጅምሩ ጀምሮ በኢትዮጵያ የብሔር አደረጃጀቶች እንዲመሰረቱና አሁን ያሉበት ደረጃ እንዲደረሱ ያደረገውን ወሳኝ ስራ ለማወቅ የኦነግና የህወሃት ወያኔ እንዲሁም ሌሎቹ የወያኔ ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አመሰራረትና እድገት ላይ የነበረውን ሚና መለስ ብሎ ማስተዋል በቂ ነው።

በህወሀት ወያኔና ኦነግ አማካኝነት የተነደፈውና አሁን ሀገራችን እምትተዳደርበት ከፋፋዩ ህገመንግስት ሲነደፍ ጀምሮ ኤርትራ ቦታ ከማመቻቸትና ከማስተናገድ ባለፈ ሻቢያ አንዱ አርቃቂ እንደነበር አይዘነጋም።

ላለፉት ሁለት አስርት አመታት ህወሃትና ሻቢያ ቴክኒካል ጠላትነታቸውን መሰረታዊ ልዩነት አስመስለው ሲሰሩት የከረሙት ድራማ ለማጠናከር በህውሃትና ኦነግ መሃከል የተፈጠረውን የስልጣን የበላይነት ሽኩቻ፤ ኦነግን ኤርትራ ውስጥ መጠለያ በመስጠት ትእይንቱን ሲያሳምሩበት እንደቆዩ አይዘነጋም።

በሁሉ ነገር ጣልቃ እየገባ የሚያተራምሰው ሻቢያ ታዲያ ኦነግን መጠለያ መስጠት ብቻ ሳይሆን በውስጥ ጉዳዩ በመግባት በሚፈልገው መልኩ ኦነግን ከከፋፈለው/ከሰነጣጠቀው በኃላ ለራሱ ኢትዮጵያን የማተራመስ አላማ ሲያሰለጥነው ከርሟል።

ህዝባዊ አመጽና ህገራዊ ትግሎች በኢትዮጵያ በርትተው ሲመጡና ወያኔ ኢህአዴግ ቅርጹን መቀየር ብቸኛ ራሱን ማዳኛ አማራጭ ሲሆንበት ወደ ስልጣን ያመጣው ጠሚ አብይም ከሻቢያ ቀጥተኛ ተጽእኖ ውጪ አይደለም። 'የኢህዴግ/ህወሃት ጠላት' መስለው በሻቢያ ሲሰለጥኑ የከረሙትን ኦነግና መሰል ድርጅቶች ያለ ቅድመ ሁኔታ ወደ ሃገር እንዲያስገባ እጁን ከመጠምዘዙም ባሻገር፤ እየፈፀሙ ላለው ጥፋት፣ አለመረጋጋት፣ ቀውስና የዜጎች ግልጽ ጥቃት ተጠያቂ ማድረግ አልቻለም። ይልቁንም እከክልኝ ልከክልህ ተባብሎ ብሄራዊ ጥበቃ እያደረገላቸው ይገኛል።

ድራማቸውን ሲሰሩ እንደሚያስመስሉት ህወሃት ብቸኛው ከይሲ ከሆነና እንደሚባለው ሻቢያ እውነተኛ ረዳት ከሆነም በጋራ ህወሃትን ማሶገድ ቀላል አማራጭ ሆኖ ሳለ ግን አይተገብሩትም። ለምን?

በተጨማሪም በሀገራችን ኢትዮጵያ ቀውሱና አለመረጋጋቱ የበዛባቸውና ከፍተኛ ችግር ውስጥ ያሉት አካባቢዎች የሻቢያን ትኩረት የሳቡትና ኢሳያስን ጨምሮ የሚመጡት ልኡኮች የጉብኝት ምርጫ የሆኑት መሆናቸውም ችላ የማይባል ሀቅ ነው።

የሻቢያ መንግስት የሀገሪቱ ቀውስ ዉስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆኑን የሚያመለክተው ሌላው መሰረታዊው ነጥብ አሁን በሀገሪቱ ያለውን የክልል አደረጃጀት አንዱን ጠላት ሌላውን ወዳጅ (ለምሳሌ ትግረይን የጠላት ቀጠና አማራን ወዳጅ) አድርጎ በመፈረጅ አለመግባባቱን እያባባሰው ይገኛል። ከዚህም ባሻገር ቅርጽ አልባ በሆነ መልኩ ኤርትራ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ክልሎች ጋር መስተጋብር መፍጠሯ ጤናማ አደለም። በተለይም ሻቢያ ከጅምሩም 'ለኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት' ሆኖ ሀገርን ከመገንጠሉ በተጨማሪ አሁን ያለው ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተጽእኖዎች ውጤት ከሻቢያ መልካም ነገር መጠበቅን የህልም እንጀራ ያደርገዋል።

ስለሆነም ወዶ ገቡ ጠሚ አብይ የራሱን ስልጣን ለማመቻቸት ሲል እያደረገው ያለው መርህ አልባና ፕሮፓጋንዳዊ ግንኙነት ሻቢያ በነጻነት የኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እጁን እንዲያስገባና እንዲፋንን ፈቅዶለታል። ይህም በመሆኑ ሃገራችን በያቅጣጫው ቀውስ ውስጥ እንድትወድቅ ከፍተኛ ሚናውን እያከናወነ ይገኛል።

Source

- https://m.youtube.com/watch?v=2JNAguSaCYA
- https://www.africanews.com/amp/2018/08/17/eritrea-president-returns-to-ethiopia-with-visit-to-amhara-region/
- https://amp.dw.com/en/ethiopias-ethnic-conflicts-destabilize-abiys-reforms/a-47035585
- https://www.latimes.com/world/la-fg-ethiopia-ethnic-violence-millions-displaced-20190530-story.html?_amp=true
- https://m.youtube.com/watch?v=m0UDvVpWrXg